## <u>በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ መንግስት የወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ</u>

- ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት /ኢዴኃኅ/
- ከኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/
- ከዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉዓላዊነት /ዓረና/ እና
- የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት /ሶዴኃቅ/

## <u>የተሰጠ መግለጫ</u>

በዓለም ላይ በየትኛውም ሀገር ያሉ የፓርቲ መሪዎች በተለያዩ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ፓርቲአቸውን ወክለው አስተያየቶችን፣ መግለጫዎችን ወዘተ ይሰጣሉ፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ሊቀመንበር የሆኑት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም የፖለቲካ ድርጅት መሪ እንደመሆናቸው በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ፖለቲካ አስቶያየቶች መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም የቀድሞው ቅንጅት አባላት / እሳቸውን ጨምሮ/፤ መንግስት ባደረገላቸው ይቅርታ ስለተፈቱበት ሁኔታ እንዲሁም የይቅርታው ጥያቄ ስለቀረበበት አግባብ ሲጠየቁ የማብራራትና መልስ የመስጠት ሕገመንግስታዊ መብት እንዳላቸው እናምናለን፡፡ ወ/ት ብርቱካንም በውጭ ሀገር ባደረጉዋቸው ስብሰባዎች በመንግስት ይቅርታ መፈታታቸውን እንዳልካዱ በሀገር ውስጥ ለሚታተሙ የመገናኛ ብዙሃን ከሰጡት መልስ ላይ ለመረዳት ችለናል፡፡ በተጨማሪም መንግስት የቀድሞው ቅንጅት አመራሮችንና አባላትን በይቅርታ ሲፈታ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ወ/ት ብርቱካን አፍርሰዋል በማለት፣ ማረጋገጫ እንዲሰጡ በተጠየቁበትም ወቅት መንግስትና ህዝብን ይቅርታ ጠይቀው መፈታታቸውን እንዳልካዱና እንደማይክዱ ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል አስረድተው መመለሳቸውን የሚገልጽ ዜና በተለያዩ የዜና አውታሮች ላይ ተጽፎ ተመልክተናል፡፡ በመሠረቱ በቀድሞው የቅንጅት አመራርና አባላት ላይ የተመሰረተባቸው ክስ "ሕገመንግስታዊውን ስርዓት በሀይል የመለወጥ ሙከራ አድርገዋል" የሚል እንደነበረ ሲታወቅ ይቅርታ የተደረገላቸውም በዚሁ የወንጀል ክስ በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ መሆኑ አይዘነጋም፡፡

በመሆኑም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፤ ዳግም በተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት ላይ ተሰማርተው እስካልተገኙ ድረስ፣ በውጭ አገር በተደረገ ስብሰባ፣ የይቅርታ ጥያቄው ስለቀረበበት ሁኔታ ከተናገሩዋቸው አረፍተ ነገሮች አንድ ሀረግ መዞ ይቅርታ "አልጠየኩም" ብለዋል በሚል ምክንያት ይቅርታው ተሰርዞ እንደገና ለእድሜ ልክ እስራት መዳረጋቸው እጅግ አሳስቦናል፡፡ ይህ የመንግስት እርምጃ በሀገራችን ውስጥ የተረጋጋ ሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር የሚካሄድበት ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ በሆነበት በአሁኑ ወቅት በመወሰዱ፣ ከመቼውም ጊዜ በላይ በአሳሳቢ ሁኔታ እየጠበበ የመጣውን የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ምህዳር ከድጡ ወደ ማጡ እንዳይከተው ከፍተኛ ስጋት አሳድሮብናል፡፡ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ወ/ት ብርቱካንና አብሮአቸው የነበሩት ዜጎች በተያዙበት ሰዓት ተወሰደ የተባለው ህገ ወጥ የሀይል እርምጃ ያደረሰው እንግልትና ጉዳት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ተይዘው ህግ ፊት መቅረብ ካለባቸው በህጉ አግባብ ከፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ አውጥቶ መሆን ሲገባ ማንነታቸውን ባላሳወቁ እና ህጋዊ መጥሪያ ባላሳዩ ሀይሎች ተገደው እየተንገላቱ መወሰዳቸው የህግ የበላይነትን የጣሰና በብዙ ወገኖች ዘንድም ስጋት የጫረ እርምጃ መሆኑ በሀገራችን ያለው ሁኔታ እጅግ አሳዛኝና አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም መንግስት ካለበት የዜጎችን መብት የማስጠበቅ ሀገራዊ ሀላፊነት አኳያ ውሳኔውን እንደገና መርምሮ እና አጢኖ የተሰረዘው የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ ውድቅ ሆኖ ቀደም ሲል የተሰጣቸው ይቅርታ ፀንቶ ከወህኒ እንዲለቀቁ እንዲያደርግ አበክረን እንጠይቃለን፡፡

- ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት /ኢዴኃኅ/
- ከኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/
- ከዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉዓላዊነት /ዓረና/ እና
- የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት /ሶዴኃቅ/

ታህሳስ 26/2001 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>